**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# ብሔራዊ ጥቅምንና

# ሀገራዊ ሉዓላዊነትን በጋራ እናስከብር!!

ሰኔ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

በተደጋጋሚ ግልፅ እንዳደረግነው በባዕዳን የሚደረገው ለወያኔ ያጋደለ፤ ወገንተኛ የሆነ ሙሉ ድጋፍ በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ መግባት፤ ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች፣ ለሀገር ሉዓላዊነት መከበር፣ ለነፃነት መጎናጸፍ፡ ለመልካም አስተዳደር ግንባታ በምናደርገው መራር ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ መቸለስ በመሆኑ አጥብቀን የተቃወምነው ወደፊትም እንዳመጣጡ የምንቃወመውና የምንታገለው ነው። የሀገርንና የጋራን ሳይሆን የባእዳንን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበርን ተንተርሶ የሚደረግ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በብዙሃኑ ሕዝብ ላይ የሚያስከትለው አደጋ በቀላሉ የማይገመት፡ መኖር የሚገባውን በዕኩልነት ላይ የሚመሠረት ግንኙነትንም የሚያሻክር በመሆኑ በቸልታ የምንመለከተው አይደለምና ሁሌም እንቃወመዋለን። የምንታገለው ኃይል የተፈለገውን ያህል እርዳታ ቢለገሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግሉን ይበልጥ ከማጠናከር አላገደውም። አገዛዙንም ከውድቀት አላዳነውም። ያለፈ ታሪካችንን ስንዳስስ በጃንሆይ አገዛዝ ዘመን ለምሳሌ በጀርመን መንግሥት የሰለጠኑና የታጠቁ የጸጥታውና የፖሊስ ኃይል በተማሪው ንቅናቄ ወቅት በዋና ዋና ተዋናይ ላይ ብቻ ሳይሆን በብዙሃኑ ተካፋዮች ላይ ያደረሱት ጉዳት በፅናት ከመታገል ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ በደም በሕይወት ክፍያ የገበየነው ተመክሮ ነውና ከቶም ልንረሳው የማንችለው ነው። በሕዝብ ትግል የአፄው ሥርዓት ተደመሰሰ። የደርግ አገዛዝም መጠነ ሰፊ እርዳታ ከያለበት ቢጎርፍለትም እሱም በተራው ከከርሰ መቃብር ከመውረድ አልዳነም።

ለወያኔ የሚለገሰው እርዳታ ዋና ዓላማው ለምዕራብ ኃያላን መንግሥታት ብሔራዊ ጥቅም አመቺ ያልሆኑ የፖለቲካ ኃይሎችን ቢቻል እንዳይጠናከሩ ማቆየት ካልሆነም ከሥልጣን ላይ እንዳይቆናጠጡ እያዳከሙ ከፖለቲካው መድረክ ማግለል ሲሆን በጎረቤት ሃገራትም እያሰማሩ ተመሳሳይ ድርጊት ማስፈፀም ነው። ወያኔ ሥልጣን ከተቆናጠጠ ጀምሮ በተለይ ጀርመን ለወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የሚሊቴሪ እርዳታ ለጋሽነት ለዚሁ ከሚጠቀሱት አንዱ ነው። በኤኮኖሚ እድገት እርዳታ ሳቢያ የራሷን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር የምታደርገው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በተፃረረ መልኩ እየተካሄደ ለመሆኑ የመለስ አገዛዝ በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው አፈና፣ ጭቆና፣ ግፍና በደል፣ ብዝበዛና ምዝበራ የሚያረጋግጠው ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ሲውጠነጠንና ሲብላላ የነበረው ሴራ ዳብሮ ደግሞ ወያኔን ለሌላ የቅጥረኛ ተግባር ላይ ለማሰማራት ዝግጅቱ ተጠናቆ ቀርቧል። ለዚህም የመለስ አገዛዝ በጀርመንና በሌሎች የምዕራብ ኃያላን መንግሥታት ግፊት 4200 የታጠቁ የጦር ወታደሮቹን በ"ሰላም አስጠባቂነት" ሥም በነዳጅ ዘይት ሀብት በበለፀገችው የአቢዬ ግዛት እንዲያሰማራ ተወስኖበታል። ወያኔ ጦሩን በሶማሌ አሰማርቶ በጦር-ወንጀለኛነት የሚያስጠይቀው ተግባር እንደፈፀመውና ውጤት አልባ ሆኖ እንደተመለሰው ሁሉ ባሁኑ ወቅትም በሱዳን የነሱ ዋነኛ ሎሌ መሆኑን በተግባር ለማረጋገጥ ተዘጋጅቷል። ወያኔን በአካባቢው የባዕዳን ብሔራዊ ጥቅም ጠባቂነት ለማሰማራት ሲባል የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በማያስጠብቅና በሀገራችን ሉዓላዊነት ላይ አደጋን ሊያስከትል በሚችል ደረጃ ማሰማራቱ ትርፉ ለመለስ አገዛዝ ብቻ እንጂ ለሕዝባችን ጠብ የሚልለት እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ከኤርትራ ጋር የተደረገው ከሙቶ ሺ በላይ ሕዝባችን ለሞት የተዳረገበት ጦርነትና  በሶማሌ የተደረገው ወታደራዊ ውጤት አልባ የጣልቃ ገብ ዘመቻ ይህንኑ የሚያምላክቱ ናቸው። ለዚህም ነው የሕዝብ ተወካዮች በይፋ ተመካክረው ሊወስኑ በማይችሉበት ሁኔታና ባንድ አምባገነን መሪ ብቻ ውሳኔ የተሰጠበትን ይህን አካሄድ መቃወም አግባብነት የሚኖረው።  የ"ሰላም ጦር"-ኡ ስምሪት ዓላማ በደቡብ ሱዳንና በበሽር አምባገነን አገዛዝ መካከል የጦር ግጭት ሳይደረግ ደቡብ ሱዳን ነፃነቷን ለማወጅ ያላትን ፍላጎት በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ነው ተብሎ በይፋ ቢገለፅም፤ ተደጋግሞ እንደተገለፀው ዋና

ምክንያቱ አሜሪካና ጀርመን በደቡብ ሱዳን የሚገኘውን የነዳጅ ዘይት ሀብት ከሰሜን ሱዳን ማዕከላዊ አገዛዝና ከተቀረው አረብ ሀገራት ተፅዕኖ ተላቆ በነሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ለማድረግ እንደሆነ ነው።

የመለስ አገዛዝ ለምዕራቡ ኃያላን መንግሥታት በአጀንዳ አስፈፃሚነት የተፈጠመ በመሆኑ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ በተለይም የጦር እርዳታ እየተለገሰው ያለው በዚሁ ምክንያት እንጂ በሌላ አይደለም። ይህም በመሆኑ በተለይ ጀርመን ከፍተኛ እርዳታ ለወያኔ እየሰጠች ያለች ብቻ ሳትሆን በአካባቢው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች። በቅርቡ የመለስ አገዛዝ T- 72 የተሰኙ ዘመናዊ ታንኮችን ከዩክሬን በውድ ዋጋ ለመግዛት እንዲያስችለው ከ100 ሚሊዮን የአሜሪካ ብር በላይ ከጀርመን እንዲያገኝ የተደረገው ምስጢሩ ይኸው እንጂ ሌላ ተአምር የለውም። ጀርመን በአፍሪካ ተግባራዊ ለማድረግ ለምትከተለው የጦር ፖሊሲ የመለስ አገዛዝን መጠቀሚያ ለማድረግና መለስ ዜናዊም ለዚህ ዝግጁ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ ከጀርመን አዲሱ የአፍሪካ የጦር ስትራተጂ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣምም በመሆኑ፤ ለኤኮኖሚ እድገት እርዳታ እየተሳበበ መጠነ ሰፊ የንዋይ እርዳታ ለመለስ መስጠቱ የሚያስገርም አይሆንም።

ይህ በጀርመንና በሌሎች ምዕራባዊያን መንግሥታት አማካኝነት ለመለስ አገዛዝ እየተሰጠ ያለው የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የጦር እርዳታ በሀገራችን እየተደረገ ያለውን የዴሞክራሲ ሂደት ክፉኛ እያደናቀፈ ከመሆኑ ባሻገር ሕዝባችን በሙብት እጦት፤ በከፋ የተጎሳቀለ ኑሮ፤ በዋጋ ግሽበት ይበልጥ እየተሰቃየ የሚገኝበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው። የመለስ አገዛዝ ከነዚሁ መንግሥታት እያገኘ ያለውን ማናቸውንም ዕርዳታ በዋናነት እየተጠቀመበት ያለው ደግሞ ለሥልጣኔ/ለአገዛዜ ያሰጉኛል በሚላቸው ተቃዋሚዎቹ ላይ በተለይም በትጥቅ ኃይል ሊፋለሙት በሚችሉት ኃይሎች ላይ እንደሆነ ያለፉት የሥልጣን ዘመኑ የሚያረጋግጡት ናቸው።

በጀርመንና በመለስ አገዛዝ መካከል ያለው የሚሊቴሪ ትብብር የሰፋ በመሆኑ እስካሁን ድረስ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የሚሊቴሪ ሥልጠና ተደርጎላቸዋል። የተወሰኑት እንዲያውም የመለስ ጦር በሶማሌ እየተዋጋ በነበረበት ወቅት የተደረገላቸው ናቸው። የወያኔ ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣናት በተለያዩ የጦር ኃይል ነክ ስብሰባዎች እንዲገኙ ተጋብዘው እንዲካፈሉ ተደርገዋል። በ2008 ዓ.ም (እአው.አ) የጀርመን መንግሥት እስከ 2011 ዓ.ም (እአው.አ) ድረስ የሚሰጥ 98 ሚሊዮን አይሮ/€ ቃል መግባቷም የሚታወስ ነው። ይኸው ትብብራቸው እየጎለበተ በመምጣቱ በያዝነው ዓመት የአየርና የምድር ጦር መኮንኖችን ሥልጠና ለመስጠት ጀርመን የሁለትዮሽ ትብብር ስምምነት ለማድረግ መነጋገሯ ተገልጧል። ለ2013 (እአው.አ) ደግሞ ዋናው ትኩረቱ በሱዳን ተግባራዊ እንዲሆን በቅርቡ ከስምምነት እንደተደረሰው ዓይነት በሰላም አስጠባቂነት ሥም በሌላ አፍሪካ አካባቢ ሊሰማራ የሚችል የጦር ኃይል ችሎታን በማዳበር ላይ ለመስማማት እቅድ ተይዟል።

በመሆኑም ይህ የነፃነታችንን ጊዜ የሚያራዝም ሂደት በአጭሩ መቀጨት ያለበት ነውና፤ ኢሕአፓ ይህንን በብሔራዊ ጥቅማችንና በሀገራዊ ሉዓላዊነታችን ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሥምሪትን አጥብቆ ይቃወማል። ሉዓላዊነቱን ማስከበር ያልቻለ ሕዝብ ደግሞ ውርደትን መከናነቡ አይቀርምና ቁርጦ ከመታገል ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም። ስለሆነም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያንም ይህንን ሁኔታ በትኩረት እየተከታተሉ የመለስ አገዛዝንና የደጋፊዎቹን ውስጣዊ ዓላማ በሚገባ በመረዳት ተቃውሚቸውን እያሰሙ ወያኔን ከሥልጣን ለማስወገድና ነፃነታቸውን ለመጎናጸፍ ቆርጠው በጋራ እንዲታገሉ ኢሕአፓ ሀገራዊ ጥሪውን ያቀርባል። በተግባርም በሀገር ቤት እንዲተባበሩትም ይጋብዛል።

እናቸንፋለን !!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France